# እሳት፡ካዬው፡ምን፡ለዬው፤

 ጥቅምት፡፳፪፡ቀን፡፪ሺ፬፡ዓመት፡ምሕረት፤




## ባንዳና፡ባንዲራውን፡ ተባብረን፡እንክላቸው።

“........የአሁኑም፡ የአብዮቱ፡መሪ፡መለስ፡ዜናዊ፡“የመናዊ፡ነኝ፤የመናዊነቴን፡አውቃለሁ።ከንጉሣዊያን፡ቤተ፡ሰብ፡በስተቀር፡ኢትዮጵያዊያን፡ዐረቦች፡ነን፡ብሎ፡ነግሮኛል።ዜናዊ፡የተባለው፡ስሙም፡የየመን፡ስም፡ነው”።

>>የሊቢያው፡መሪ፡ኰሎኔል፡ጋዳፊ።<<ሰኔ፡፲፫፡ቀን፡፲፱፻፹፫፡ዓመተ፡ምሕረት።{ኢትዮጵያና፡ዕድሏ።በ፡ኮ/አሥራት፡ቦጋለ}።

ከ፡፲፱፻፷፬፡እስተ፡፲፱፻፺፩፡ዓመተ፡ምሕረት፡ያሳለፍነው፡ግዜ፡የጭንቅ፤የሥቃይና፡መከራ፡ወቅት፡እንደ፡ነበረ፡የማይረሳ፡ለዘላለም፡የሚታዎስ፡ነው።በአሁኑ፡ዓለማት፡በተሻሻሉበት፡ዘመን፡ይፈጸማል፡ተብሎ፡የማይታሰበውን፡ጨካኙና፡አረመኔው፡መንግሥቱ፡ኃይለ፡ማርያም፡ሰላማውያኑን፡ለሀገራቸው፡ደማቸውን፡ያፈሰሱ፤አጥንታቸውን፡የከሰከሱ፡ጀግና፡ሕዝቦች፤ብልህ፡ተማሪዎችን፡ወንድ፡ሴት፡ሳይለዩ፡ከግፈኛው፡ለገሠ፡አስፋውና፡ዓለሙ፡አበበን፡ከመሳሰሉት፡ሰይጣናሞች፡ጋራ፡በመተባበር፡ቀይ፡ሽብር፡በሚል፡የተረሣ፡ፍልስፍና፡መሠረት፡በማድረግ፡ጨፈጨፏቸው።መከራ፤ችግርና፡ሥቃይ፡እንዲፈጸምባቸው፡አደረጉ።በኋላም፡መንግሥቱ፡ወደ፡ዚምበብዌ፡ሸሸ።ከእርሱ፡በኋላ፡የተተካው፡ሰይጣኑ፡ከሃዲው፤የከሃዲ፡ልጅ፡ዘረ፡ከሃዲ፡ለገሠ፡ዜናዊ፡ደግሞ፤ከነገር፡አባቱ፡ስብሐት፡ወልደ፡ሥላሴ፡ነጋና፡አጐብዳጅ፡ጓደኞቹ፡ከነ፡በረከት፡ስምዖንና፡ሌሎችም፡ልክስክስ፡አጋንንት፡የወያኔ፡ትግሬዎች፡ጋራ፡በመተባበር፡ሕዝቡን፡በልዩ፡ልዩ፡ዘዴ፡በችግርና፡በረሃብ፡እንዳልነበረ፡ቁም፡ስቅሉን፡እያሳዩት፡ነው።የሚገርመው፤በጐረቤቶቻችን፡የመንና፡ግብፅ፡እልፍ፡ብሎም፡ቱኒዚያና፡ሊቢያ፡የደረሰውን፡ተመልክተው፡አለመ

ታረማቸው፡ነው።

ከዓለም፡ባንክ፡ለልማት፡ከተገኘው፡ብድር፡ከምዕራብና፡እሩቅ፡ምሥራቅ፡አገሮች፡ከተሰጠው፡የዕርዳታ፡ገንዘብ፡ከ፡፻ው፡፸፭ቱን፡ዘርፈው፡በውጭ፡አገር፡ባንኮች፡በስማቸው፡ያስቀመጡ፡መሆናቸውን፡ማንም፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ሊያውቀው፡ይገባል።የምሥጢር፡ቁልፋቸው፡የነበረውን፡ክንፈ፡ገብረ፡መድኅንን፡አረመኔው፡አንባገነን፡ለገሠ፡ዜናዊ፡በጸጥታ፡ሰዎቹ፡ካስገደለው፡በኋላ፡የምሥጢር፡መዛግብትና፡ጽሑፎችን፡የሰበሰበና፡የወሰዳቸው፡እርሱ፡እራሱ፡መሆኑን፡እንዳይረሳ።ይህን፡ያደረገውም፡አረመኔያዊ፡ሥራው፡እንዳይታወቅበት፡ማስረጃ፡ለማጥፋት፡ነው።ዳሩ፡ግን፡ወደ፡ፊት፡በሕግ፡መጠየቁ፡ስለማይቀር፡በተለመደው፡አለብላቢት፡ምላሱ፡ለመካድ፡አይሞክር።ግዜው፡ቅርብ፡ነውና፡ወዮለት!!።

የጭካኔና፡የክፋት፡ሥራው፡አይረሳም።በተለይ፡ከትግሬ፡ሕዝብ፡ነጥሎ፡የሚመለከታቸውን፡የአማራን፤የኦሮሞን፤የጉራጌንና፡የደቡብ፡ሕዝቦችን፡በድህነት፤በችግርና፡በረሃብ፡በማሠቃየት፡ሲፈጽም፤ዛሬ፡ደስታው፡ነው።በአንድ፡ጐሣ፡የበላይነት፡ሙብትህን፡የተነፈግኸው፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ሆይ!፡በምን፡ዓይነት፡አስተዳደር፡ግድለት፡እንደምትሰቃይ፡ዜናውን፡ሰማነው።“Bad news for property owners in Ethiopia: No more home and land ownership. Instead, owners are allowed to lease their own property.”እንዴት፡በዝምታ፡ትመለከተዋለህ??።ምንስ፡ቀረህ??።የቤትህ፤የመሬትህ፤የሀገርህ፤የዜግነትህ፡ወ.ዘ.ተ.........መብትህ፡ተነጥቆ፡እንደ፡ፈለጉት፡እያደረጉህ፡ነውኮ!!።እስተመቼ!!!???።የአንባገነኖችን፡አወዳደቅ፡አንብበናል።ዓይተናልም።ሕዝብን፡አሠቃይቶ፡እራስን፡ማበልፀግ፡ለማንም፡አልበጀም/አይበጅም።“የወደቀ፡ዛፍ፡ምሳር፡ይበዛበታል”።እንደ፡ተባለው፡ዛሬ፡በማይጨበጥ፡ንግግሩ፡እያታለለ፡ያጐበደደላቸው፡መንግሥታት፡ግዜው፡ደርሶ፡አወዳደቁ፡መላ፡በሚያጣበት፡ወቅት፤የሙባርክና፡ጋዳፊ፡ዕድል፡ነው፡የሚጠብቃቸው።ያ፡እንዲሆን፡ደግሞ፡ያንተን፡ታጋሽ፡ጸሎተኛ፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ቆርጦ፡መነሣት፡ይጠይቃል።እነ፡ሙባረክ፡በቢሊዮን፡የሚቆጠር፡ከሕዝቡ፡የወሰዱት፡ገንዘብ፡እንዲመለስ፡እዬተደረገ፡ነው።ለገሠ፡ዜናዊም፡እበላዋለሁ፡ብሎ፡ያሥባል!!??።አዬ!፡ከንቱ፡ሐሣብ፡ነው።የዘረፈው፡ገንዘብ፡ለሕዝቡ፡በሕግ፡እንዲመለስ፡የሚደረግ፡መሆኑን፡ሳይጠራጠር፡አውቆት፡ይቆይ።በሥልጣን፡ተጨማልቆና፡ግባሶ፡የምክር፡ቤት፡አባሎቹም፡የጻያፍ፡ቃላቶቹን፡ስድብ፡ሰምተው፡እጃቸውን፡ሲቀስሩ፡ይውላሉ።ምንም፡ዓይነት፡ቅሬታ፡ሳይሰማቸው፡አታሎ፡የሚኖረው፡ለገሠ፡ዜናዊን፡ሲያደንቁ፡አያፍሩም።ምን፡ይደረግ!።“ከአህያ፡የዋለች፡ጊደር፡ሌላ፡ጠባይ፡ትማራለች”።እንደተባለው፡ከእርሱ፡ጋራ፡ውለው፤ምን፡ሊያፈልቁ፡ይችላሉ?።እንደዚህ፡እራሳቸውን፡እያታለሉ፡ሆዳቸውን፡ይሙሉ።እርሱም፡ሆነ፡አጐብዳጆቹ፡የሰው፡ሳይሆን፡እግዚአብሔር፡ይፋረዳቸዋል።

የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ሆይ!፤ዝም፡ብለህ፡አትመልከታቸው።በዝምታና፡ቸልተኝነት፡ትምክህተኛን፡ማሳለፍ፡አይገባም።ጠላትህ፡አረመኔው፡አንባገነን፡ለገሠ፡ዜናዊ፡እስቲንበረከክልህ፡ተነሣና፡አጣድፈው።የሕዝብ፡ኃይል፡ሁልግዜም፡ያሸንፋል።ለአገሩ፡ነፃነት፤ለሕዝባዊ፡አገዛዝ፡መሥዋዕት፡መሆን፡ይገባል።ፍልስጥኤማውያንን፡ምሳሌ፡በማድረግ፡እንዳያዘናጋህ፡ተጠንቀቅ።በደቡብ፡የዋካና፡ዳውሮ፡ሕዝብ፡ሰሞኑን፡የሚያደርገውን፡እንቅስቃሴ፡ከመደገፍ፡አትቆጠብ።በዬቦታው፡ሰላማዊ፡ትግሉንም፡እያፋፋምህ፡አይዞህ፡በርታ።ሁሉ፡በጅህ፡ሁሉ፡በደጅህ፡ነው።ኅብረት፡ካለ፡ድል፡አለ።መከፋፈል፡ካለ፡መሰባበርና፡መሸነፍ፡ነውና፡ምርጫህ፡ኅብረት፡ይሁን።

# ኢትዮጵያ፡ታሪኳንና፡ሉዓላዊነቷን፡አስከብራ፡ለዘላለም፡ትኖራለች።

እ፡ጦማር፡- zienamarqos@yahoo.com ከዜናማርቆስ፡መርሐ፤ካናዳ።